የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**ይፋዊ መግለጫ**

**ጉዳዩ፡ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ ስላልተሰጠው ታኪሎ "ኢንቨስትመንት ባንክን" በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያን ይመለከታል**

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ታኪሎ "ኢንቨስትመንት ባንክ" በሚል ስም የሚንቀሳቀስ ፈቃድ ያልተሰጠው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት መለየቱን ለህብረተሰቡ ለማሳወቅ ይወዳል። ይህ አካል አስፈላጊው ፈቃድ ሳይኖረው በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኢንቨስትመንት ባንክ ነኝ በሚል ድረ-ገጽ አቋቁሟል። ታኪሎ "ኢንቨስትመንት ባንክ" በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት የኢንቨስትመንት ባንክም ሆነ ሌላ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ለመሆን የሚያስፈልገውን ፈቃድ ያላገኘ በመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የካፒታል ገበያ አገልግሎት እንዲሰጥ ያልተፈቀደለት አካል መሆኑን የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን አፅንዖት ይሰጣል።

በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 መሰረት የካፒታል ገበያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አገልግሎት እንዲሰጡ በህጋዊ መንገድ በየኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣንን የተመዘገቡ እና የሚተዳደሩ አካላት ብቻ ናቸው። ስለሆነም ግለሰቦች እና ድርጅቶች ከዚህ አካል ወይም ከኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ተገቢውን ፈቃድ ካላገኙ ሌሎች "የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች" ጋር በማናቸውም አይነት የካፒታል ገበያ ነክ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች እንዳይሳተፉ በጥብቅ ይመከራሉ።

እነዚህ አካላት ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ እና የገበያ ታማኝነትን(integrity) ለማረጋገጥ በተነደፈው የቁጥጥር ስርዓት ስለማይገዙ ከእንደዚህ አይነት ፈቃድ ካልተሰጣቸው አካላት ጋር መስራት ኢንቨስተሮችን ለከፍተኛ አደጋ ሊያጋልጥ ይችላል። ኢካገባ ህብረተሰቡ ማንኛውም ራሱን እንደ ካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ከሚያቀርብ ግለሰብ ወይም ድርጅት ጋር ስምምነቶች ወይም ግብይቶችን ከመፈጸሙ በፊት የብቁነት እና የፈቃድ ሁኔታውን እንዲያረጋግጥ ያበረታታል።

እንዲሁም ሁሉም ግለሰቦች እና ድርጅቶች ማንኛውንም የኢንቨስትመንት እድሎች ለመጠቀም በሚያስቡበት ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያሳስባል። ስለ አገልግሎት ሰጪው ህጋዊነት ወይም ስላገኙት የኢንቨስትመንት እድል ጥርጣሬ ካሎት፣ እባክዎን የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣንን ያግኙ ወይም መመሪያ ለማግኘት እና ለማረጋገጥ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣንን ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ እና የኢትዮጵያን የካፒታል ገበያን ደህንነት እና ታማኝነት ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው።በመሆኑም ያልተፈቀደላቸው አገልግሎት ሰጪዎች እንቅስቃሴዎችን ለመግታት እና ለመከላከል አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

ህብረተሰቡ ያልተፈቀዱ ተግባራትን በሚመለከትበት ጊዜ ለየኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣንን እንዲያሳውቅ እናበረታታለን። ለተጨማሪ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ እባክዎን የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን የሚከተሉትን አድራሻዎችን ይጠቀሙ።

**አድራሻ**

ኢሜል፡ communications@ecma.gov.et
ድረ ገጽ፡ ecma.gov.et

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**Public Notice**

**Subject: <u>Warning about an Unauthorized Capital Market Service Provider - Takilo "Investment Bank"</u>**

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) wishes to inform the public that it has identified an unauthorized capital market service provider, operating under the name Takilo "Investment Bank", This entity has set up a website claiming to be the first investment bank in Ethiopia providing capital market services, without the required license.

ECMA emphasizes that Takilo "Investment Bank" has not acquired the required license to be an investment bank or any other capital market service provider as per the requirements set under the Capital Market Service Providers Licensing and Supervision Directive No. 980/2024 and hence is not authorized to provide capital market services within Ethiopia.

According to the Capital Market Proclamation No. 1248/2021 and the Capital Market Service Providers Licensing and Supervision Directive No. 980/2024, only entities duly registered and regulated by the ECMA are legally permitted to provide capital market services in Ethiopia. Therefore, Individuals and organizations are strongly advised not to engage in any form of capital market related investment transactions with this entity or any other "capital market service provider" that has not been duly licensed by the ECMA. Engaging with such unauthorized entities may expose investors to significant risk, as they are not subject to regulatory oversight designed to protect investors and ensure market integrity. The ECMA encourages the public to verify the credentials and licensing status of any individual or organization posing as a capital market service provider before entering into any agreements or transactions.

We also remind all individuals and organizations to exercise caution and due diligence when considering any investment opportunities. If there is uncertainty about the legitimacy of a service provider or investment opportunity, please contact the ECMA or visit our official website for guidance and verification.

The ECMA is committed to protecting investors and ensuring the safety and integrity of Ethiopia's capital markets. We will take necessary actions to address and prevent the operation of any unauthorized service providers. We also encourage the public to report any unauthorized activities to ECMA.

For further inquiries or to report concerns, please contact the Ethiopian Capital Market Authority at:

**Contact Information**
Email: communications@ecma.gov.et
Website: ecma.gov.et